# የገንዘብ ሚኒስቴር

# MINISTRY OF FINANCE

## ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የሚሆኑ እቃዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1006/2016

**DIRECTIVE NO. 1006 /2024**
**A DIRECTIVE TO PROVIDE GOODS EXEMPT FROM VALUE ADDED TAX No. 1006/2024**

# ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የሚሆኑ እቃዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1006/2016

ዝቅተኛ ገቢ ያለው የህብረተሰብ ክፍል መሰረታዊ የሆኑ የምግብ አቅርቦቶችን ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ ሆኖ እንዲገዛ ማድረግ የወጪ ጫናውን በማርገብ ረገድ ጠቀሜታ ያለው መሆኑ ስለታመነበት፤

ከዚህ በፊት በተለያዩ መመሪያዎች እቃዎች በጥቅል ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ መደረጋቸው ተጠቃሚ እንዲሆን የታሰበውን የህብረተሰብ ክፍል የማይጠቅም እርምጃ ሆኖ ከመገኘቱም በላይ የመንግስትን ገቢ በመሸርሸር መንግስት የድሃውን ህብረተሰብ ህይወት የሚለውጡ የማህበራዊ እና ኤኮኖሚያዊ ልማት ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል ገቢ እንዳይኖረው ያደረገ በመሆኑ፤

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ (2) 4 ለገንዘብ ሚኒስቴር በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚከተለው መመሪያ ወጥቷል።

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ **"ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የሚሆኑ እቃዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1006/2016"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ ስለማድረግ

1) በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 8 (2) እና በተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 19 እስከ 33 ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በሆነው ሰንጠረዥ የተዘረዘሩት በአገር ውስጥ የሚመረቱ እና ከውጭ አገር የሚገቡ እቃዎች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ ተደረገዋል።

# A DIRECTIVE TO PROVIDE GOODS EXEMPT FROM VALUE ADDED TAX DIRECTIVE NO. 1006/2024

WHEREAS, it is believed that exempting basic food items from the Value Added Tax will help ease the financial burden of low-income group of the society;

WHEREAS, the blanket exemption from Value Added Tax previously granted to goods through various directives did not effectively benefit the intended sections of society, but instead reduced government revenue that could have been utilized for economic and social development activities to change the lives of the poor;

NOW THEREFORE, in accordance with the power vested in the Ministry of Finance under Article 8 sub article 2(4) of the Value Added Tax Proclamation No.285/2002 (as amended), the following Directive is issued.

## 1. Short Title

This directive may be cited as "**A Directive to provide goods exempt from Value Added Tax No.1006/2024**"

## 2. Exemption from Value Added Tax

1) In addition to goods listed under Article 8(2) of the Value Added Tax Proclamation No 285/2002 (as amended) and Article 19 to 33 of the Value Added Tax Regulation No. 79/1995, goods produced locally and imported from abroad listed in the Annex to this Directive shall be exempt from Value Added Tax.

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ከተመለከቱት ውጪ ከዚህ በፊት በተለያዩ ጊዜያት ከገንዘብ ሚኒስቴር በተላለፈ መመሪያ ወይም ውሳኔ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ ተደርገው የነበሩ እቃዎች እና አገልግሎቶች ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የተጨማሪ እሴት ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡

3) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የተደረጉ እቃዎችን እና አገልግሎቶችን እንዲሁም የተጨማሪ እሴት ታክስ አከፋፈል ስርአትን በተመለከተ በገንዘብ ሚኒስቴር የተላለፉ ውሳኔዎችን አይጨምርም፡፡

## 3. <u>ስለመሻር</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2 (1) እና (3) ከተመለከቱት በስተቀር እቃዎች እና አገልግሎቶች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ እንዲሆኑ ከ1994 ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት በገንዘብ ሚኒስቴር የተላለፉ መመሪያዎች እና ውሳኔዎች ይህ መመሪያ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ተሽረዋል፡፡

## 4. <u>የሚጸናበት ቀን</u>

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በገንዘብ ሚኒስቴር እና በፍትህ ሚኒስቴር ድረገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ 13 ቀን 2016 ዓ.ም
አህመድ ሺዴ
የገንዘብ ሚኒስትር

2) With the exception of goods mentioned under sub article 1 of this Article, all goods and services that have been exempt through various Directives issued or decisions made by the Ministry of Finance heretofore shall be subject to Value Added Tax as of the date in which the Directive enters into force.

3) The provisions of sub-article 2 of this Article shall not apply to decisions made by the Ministry of Finance with respect to goods and services that are exempt under international agreements to which Ethiopia is a party as well as to arrangements made for payment of Value Added Tax.

## 3. <u>Repeals</u>

All directives issued and decisions made as of the year 2002 by the Ministry of Finance, with the exception of those stated under sub article (1) and (3) of Article 2 of this Directive, in connection with the exemption to goods and services from Value Added Tax shall be null and void as of the effective date of this Directive.

## 4. <u>Effective Date</u>

This Directive shall enter in to force on the date of its registration by Ministry of Justice and posted on the website of the Ministry of Justice and the Ministry of Finance.

Done at Addis Ababa this day of June 20, 2024

Ahmed Shide
Minister of Finance

## አባሪ 1
## ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የሆኑ እቃዎች እና አገልግሎቶች ዝርዝር

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 8 (2) እና እና በተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 19 እስከ 33 ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በአገር ውስጥ የሚመረቱ እና ከውጭ አገር የሚገቡ እቃዎች እንዲሁም በአገር ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ መሆናቸው ይቀጥላል::

1) እህል እና ጥራጥሬ
   - (i) ጤፍ፣
   - (ii) ስንዴ፣
   - (iii) ገብስ፣
   - (iv) በቆሎ፣
   - (v) ማሽላ፣
   - (vi) ዘንጋዳ፣
   - (vii) ዳጉሳ ፣
   - (viii) አጃ፣
   - (ix) አተር፤ ባቄላ፤ ምስር፤ አኩሪ አተር፤ ሽምብራ፤ ግብጦ፤ ጓያ እና የመሳሰሉት ጥራጥሬዎች፤ እና
   - (x) የእነዚህ ዱቄት::
2) የግብርና ግብአቶች
   - (i) ማዳበሪያ፣
   - (ii) ጸረ-ተባይ ኬሚካል፣
   - (iii) ምርጥ ዘር፣
   - (iv) የእንስሣት መድሃኒት፣ እና
   - (v) የመድሃኒት መርጫ::
3) የበሰሉ ወይም የተዘጋጁ ምግቦች/ መጠጦች
   - (i) እንጀራ
   - (ii) ዳቦ
   - (iii) ወተት
4) በካፒታል ሊዝ ስምምነት የሚቀርቡ የካፒታል እቃዎች
5) የወባ መከላከያ አጎበር፤ ኮንዶም እና ለውሃ ማከሚያ የሚሆኑ ኬሚካሎች::

## Appendix 1
## List of goods and services exempt from value added tax

In addition to those listed under Article 8 (2) of the Value Added Tax Proclamation No. 285/1994 and Article 19 to 33 of the Value Added Tax Regulation No. 79/1995, goods produced in the country and imported from abroad as well as services provided in the country will continue to be exempt from the value added tax.

1) Cereals and pulses
   - i. Teff,
   - ii. Wheat,
   - iii. Barley,
   - iv. Maize
   - v. Sorghum,
   - vi. Zengada (Ethiopian millet),
   - vii. Dagusa (Finger millet),
   - viii. Oats,
   - ix. peas; beans, lentil, soyabean; chickpeas፣ lupin bean (gebeto), *Grass pea (lathyrus sativus)* and other similar grains; and
   - x. Powder of these.
2) Agricultural inputs
   - i. fertilizer,
   - ii. Pesticides,
   - iii. Seed,
   - iv. Veterinary medicine, and
   - v. Drug sprayer.
3) Cooked or prepared foods/drinks
   - i. Injera,
   - ii. Bread, and
   - iii. Milk.
4) Capital goods provided by capital lease agreement
5) Anti-malarial mosquito net; condom and chemicals for water treatment.